# የትግራይ ህዝብ ሆይ፤ *ሀገር ሳትሰበር ዝምታው ይሰበር!*


ሚካኤል ፡ ከአዲስ አበባ

(Michael_zeab@yahoo.com)


የትግራይን ህዝብ ዝምታ በተመለከተ ቀደም ሲል የተለያዩ ጽሁፎች አንብበናል። በቅርቡ እንኳን በጀነራል ሀይሌ መለስ የተጻፈ ሰፊና ጥልቀት ያለው ጽሁፍ አውሮፓና አሜሪካ ያሉ ወዳጆቻችን በኢሜይል ልከውልን ለማንበብ ችለናል። እዚህ ሀገር ቤት ውስጥ ያለውም አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በልቡ ይጠይቃል፡ ያብሰለስላል - የትግራይ ህዝብ ምነው ዝም አለ? የገዛ ሀገሩ ከአብራኩ በወጡ ከሃዲዎች ስትፈርስ ፣ በዘር መርዝ ስንበታተን ፣ ማንነታችንን ስናጣ ፤ የትግራይ ጎሳ ተወላጆች እንዴት ጭጭ አሉ? ዝምታውስ እስከመቼ? ምን እስክንሆን? ቀሪው ወገኑ በወያኔ መሪነትና በእበላ ባይ ጅቦች ሌት ተቀን ሲሰቃይ ፣ የሚላስ የሚቀስ አጥቶ ኑሮ መከራ ሲሆንበት ፣ ሲታሰር ፣ ሲሰደድና ሲገደል፤ በርግጥ የትግራይ ህዝብ ጎረቤት ሀገር ይመስል ምነው ዝም አለ? ወንድማማቾች አይደለንምን? ሌላው ህዝብ ወገኑ አይደለምን? አማኝ ለሆኑቱስ የምድሩ ቢቀር በሰማይ አያስጠይቅምን?

በርግጥ ይህ ጥያቄ የትግራይ ህዝብ ላይ የሚነሳው እነሱ ከሌላው ኢትዮጵያዊ የተለየ ፍጡር ስለሆኑ አይደለም። ወይም ደግም ትግሬ በሙሉ ወያኔ ነው ከሚል ጭፍን አስተሳሰብም አይደለም። ይልቁንም ሌላው ወገኑ በአራቱም ማእዘን ለነጻነቱ ፣ ለመብቱና ለእናት ሀገሩ ሌት ተቀን ሲታገል የትግራይ ህዝብ ግን በተመሳሳይ ሲተጋ ባለመታየቱ ነው። ይሄ ለምን ሆነ?

ሌላው ህዝብም ወያኔን አምርሮ የሚታገለው ከትግራይ ህዝብ በላይ ኢትዮጵያዊ ነኝ ከሚል ግብዘነትም አይደለም። ለነገሩማ ለኢትዮጵያችን አንድነትና ምንነት ከትግሬ በላይ ማን? በታሪክ እንደምናውቀው የትግራይ ህዝብ ለሃገሩና ለሀይማኖቱ ሟች ነው። ዛሬ ግን ሀገር በጎሳ ስትበጣጠስና እንደ ሱማሊያ ለመበታተን ስታኮበኩብ ፤ ሌላው ቀርቶ ልባቸው በሃዘን የሚደማ የትግራይ ተወላጆች እንኳን፡ ያንን ለማስቆም ሲታገሉ አይታይም። አያት ቅድም አያቶቹ ደማቸውን ያፈሰሱላት አጥንታቸውን የከሰከሱላት ሃገር፡ ከአብራኩ በወጡ መሰሪዎች ስትደረመስ ጭጭ ብሏል። እነመለስ አማራ ወይም ኦሮሞ ወይም ጣሊያን ወይም ድርቡሽ ቢሆኑ ኖሮ የትግራይ ህዝብ እንዳሁኑ ዝም ይል ነበርን? ከትግራይ ህዝብ ጉያ ስለወጣ ወያኔ የሁላችንም መጠለያ የሆነችውን ሀገራችንን የማፍረስ መብት ይሰጠዋልን?

ይህ ወቅታዊና አንገብጋቢ ጥያቄ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ፡ በጣት የሚቆጠሩ የትግራይ ልጆች ከሚያደርጉት ቆራጥ ሀገራዊ ትግል ውጭ፡ አብዛኛው ትግሬ በጸጥታው ገፍቶበታል። ይልቁንም ከፊሉ "ጊዜው የኛ ነው በልተን እንሙት" በሚል ራስ ወዳድነትና የነገን ማየት በተሳነው ጭፍንነት (myopia) የገዛ ወገኑ ላይ ግፍ ይፈጽማል ፣ ያስፈጽማል ፣ ይተባበራል። በዚህም ምክንያት በትግራይ ህዝብና በተቀረው ኢትዮጵያዊ መካከል ያለው የልዩነት ድልድልይ ከግዜ ወደግዜ በሚያስፈራ ሁኔታ እየሰፋና እየገዘፈ ሄዷል። መቀረራብ ፣ መተማመናን መደማመጥ የማይቻልበት ሁኔታ ላይ እየደረስን ነው። በመሃከላችን የዘር ግንብ ገንብተው አንዳችን ሌላችንን በጥርጣሬና በጥላቻ እንድናይ እያደረጉን ነው። የኤርትራ ሲቆጨን ዛሬ ደግሞ መለስና ቡድኑ የትግራይን ህዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ለመለየት ሌት ተቀን ይተጋሉ። የትግራይ ልጆችም በዝምታ ቆመው ያያሉ ፡ ከፊሎቹም ያግዛሉ።

በዚህ ጉዳይ ዙሪያ እንደ አንድ ዜጋ የታዘብኩትንና እንዳይከሰት የምሰጋውን ችግር ለትግራይ ወገኖቼ ላወጋቸው ወደድኩኝ። ይህን የማደርገው ምናባክ የታባክ ልክ ልክህን ነገርኩህ ለሚል የጅል ቀረርቶ ሳይሆን፡ ያለውን ሃቅ ተነጋግሮ መፍትሄ ቢመጣ ይሻላል፤ ትግሬ ወንድሞቼም ወደ ህሊናቸው ተመልሰው ጥያቄ እንዲጠይቁ ያስችላቸው ይሆናል ከሚል ቀና ሃሳብ በመነሳት ብቻ ነው። እኛስ ደፍረን ካላወራነው ማን ይመጣልናል?

በርግጥ የትግራይን ህዝብ በሙሉ በአንድ ቅርጫት ውስጥ አስቀምጦ ማየት እንደ ወያኔ ዘረኛ ከመሆንም በላይ ስህተት ላይም ይጥለናል። እንደኔ እይታ በትግራይ ውስጥ የሚኖረው የትግራይ ህዝብና በሌሎች አካባቢዎች የሚኖረው ትግሬ ዝምታው ወይም ድጋፉ የሚመነጨው ከተለያዩ

ምክንያቶች ነው። ስለሆነም በቀሪው ጽሁፌ እነዚህን ምክንያቶች በሁለት ከፍየ አስረዳለሁ - ትግራይ ውስጥ ያለ ትግሬ ኢትዮጵያዊና ከትግራይ ክልል ውጭ በሌሎች ክልሎች የሚኖረው ትግሬ ኢትዮጵያዊ። ምንም እንኳን መረጃዎቹ ለአንዳንድ የዚህ ጽሁፍ አንባቢዎች አዲስ ባይሆኑም እውነት ናቸውና፤ በሰፊው ህዝብ ልብ ውስጥ የሚጉላሉ ናቸውና ተደግመው መነገራቸውም ተገቢ ነው እላለሁ። *ችግሩ ስር እየሰደደ እንጂ ለውጥ እያየን ስላልሆነ* በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ደጋግሞ መወያየቱ አንገብጋቢ ነው ብዬ አምናለሁ።

## *1) **ትግራይ ውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ*** - የተበደለ ህዝብ ለምን ዝም ይላል?

ትግራይ ውስጥ ያለው ጭቁን ገበሬ ኦሮሚያና አማራ ወይም ሌላ ክልል ውስጥ ካለው ኢትዮጵያዊ ገበሬ የተለየ ነው የሚል ሰው ያለ አይመስለኝም። እዛ ክልል ውስጥ ያለ ዜጋ ኢትዮጵያዊነቱን ክዷል ብሎ የሚከራከርም የለም። አሁንም ድረስ ትግራይ ውስጥ ሰው ሲሞት ለገዢዎቻችን "ጨርቅ" በሆነው በኢትዮጵያ ባንዲራ ተጠቅልሎ ነው ወደ ከርሰ መቃብር የሚገባው። ታዲያ አማራው፣ ኦሮሞው፣ ወላይታው፣ ጉራጌው…ሁሉም በአንድነት ሲታገል ምነው የትግራይ ወገናችን ድምጹን አያሰማ? ለዚህ 4 ምክንያቶች ማስቀመጥ ይቻላል።

### ***ሀ) ትግራይ ውስጥ ነጻነት የሚባል ነገር የለም - ይልቁንም ዘረኝነት አለ!***

ትግራይ ውስጥ ነጻነትና ዲሞክራሲ የሚባሉ ነገሮች የማይታሰቡ ናቸው። እንደሚባለውም የትግራይ ክልል ህዝብ በወቅቱ በወያኔ አፈ-ሙዝ ስር ስለሚገኝና ነጻም ስላልሆነ ነው እንጂ እንደውም ዋናው ተጠቂና የገፈቱ ቀማሽ እሱ ነው። ለዚህም አንድ ጥሩ ማስረጃ የክልሉ ህዝብ የሌሎቹ ወገኖቹን ያክል እንኳን ነጻ ጋዜጣ እንደልብ ማንበብ እንደማይችል ይታወቃል። በዚህም ምክንያት ወያኔ ሌት ተቀን ከሚመግበው የውሸት ፕሮፓጋንዳ ያለፈ ሌላው ወገኑ ላይ የሚደርሰውን ግፍ ለማየት ቀርቶ እዛው ክልል ውስጥ እንኳን የሚፈጸመውን አድሎና በደል ማየት ይከብደው ይሆናል።

እውነታው ግን ትግራይ ክልል ውስጥ አይን ያወጣ ዘረኝነት አለ። በስልጣንና በሃብት የበለጠ ተጠቃሚዎቹ የተመረጡና ጥቂቶች **አሽአ** በሚል ምህጻረ ቃል የሚታወቁት የአድዋ ፣ የሽሬ እና የአክሱም ተወላጆች ብቻ ናቸው። ከትግራይ አካባቢዎች ሁሉ ይበልጥ በልማት ተጠቃሚ የሆኑትም እነዚህ ቦታዎች ናቸው። አብዛኛዎቹ ፋብሪካዎች የተከፈቱት በተለይም አድዋ ውስጥና እነዚህ አካባቢዎች ነው። በንፅፅር በሌሎቹ የትግራይ አካባቢዎች ከትናንሽ ፕሮጀክቶች የዘለለ እዚህ ግባ የሚባል ነገር አይታይም።

የሌላው አካባቢ ትግሬዎች በነዚህ የበለጠ ትግሬ ነን በሚሉ ዘረኞች ይናቃሉ። **አሽአዎች** ሌላው ትግሬ ላይ አመኔታም የላቸውም። ዩኒቨርስቲ እያለን አንድ የእንደርታ ልጅ፡ በተለይም የአድዋ ሰዎችን ትምክህተኝነት፡ የበላይነትና እነሱ በሌላው ትግሬ ላይ የሚፈጽሙትን መድሎ፡ አምርሮ ያጫውተኝ ነበር። በፌደራልም ሆነ በክልል ያሉ ቁልፍ ቦታዎችን የያዙትም በዝምድናና በጋብቻ የተሳሰሩ የነዚህ ምርጥ ዘር ነን ባይ ሰዎች እንደሆኑም ይታወቃል። ዘረኝነት እኮ በሽታ ነው። እየወረደና እየቀጠነ ሁሉንም በየተራ ይለክፋል። መድሀኒቱም በዘር ማሰብ አቁመን ሰው መሆን ብቻ ነው። "እምቢ ለዘረኞች" ብለን በአንድነት እንቁም የሚባለውም ለዚህ ነው።

### *ለ) **የትግራይ ልማት** - ለህዝቡ ታስቦ ወይስ ለወያኔ የፖለቲካ ጥቅም?*

በአንጻራዊ መልኩ የትግራይ ክልል ከሌሎቹ የኢትዮጵያ ክልሎች በተለየ አላደገም ብሎ መከራከር ሃቅን መሸሽ ይሆናል። ይሄም ስለተባለ የሚከፋ ትግሬ ሊኖር አይገባም። እንደትግራይ መንገድ የተሰራለት፤ ፋብሪካዎች የተከፈቱበት፤ ትምህርት ቤቶች የተገነቡለት የቱ ክልል ነው? እንደድሮው እዛ አካባቢ የረሃብና የድርቅ ወሬ እንኳን አሁን የለም። ጥያቄው ግን ወያኔ ይሄንን የሚያደርገው ለምንድን ነው?

የመጀመሪያው መከራከርያ በትግሉ ወቅት ብዙ የተጎዳ ህዝብ ስለሆነ የበለጠ መጠቀም ይገባዋል የሚል ነው። ይሄ ደግሞ እስከመቼ የሚል ጥያቄ ያስነሳል - ጠንከር ሲልም "ትግራይ እስክትለማ ሌላው ሃገር ይድማ" ነው ወይ? አስብሏል። ይልቁንስ በርግጥ በጦርነቱ የተጎዳው የትግራይ ክልል ብቻ ነውን? በርግጥ ደርግን ለመጣል ልጁንና አባቱን የገበረው ትግሬ ብቻ ነውን? የሚሉ

ጥያቄዎችን ያስነሳል። በሌላ በኩል ወያኔና ጀሌዎቹ በትግራይ ህዝብ ስም ዘርፈው ለራሱ ለትግራይ ህዝብ በማንኪያ ቆንጥረው ከሚሰጡት ይልቅ እነሱ ባካፋ ወደግል ኪሳቸው የሚያስገቡት እንደሚበልጥ ይታወቃል። መጨረሻ ላይ ለህዝቡ የሚተርፈው ከሌላው ወገኑ ጋር መባላቱ እንጂ እነሱ አንድ ቀን ያበጠ ቦርሳቸውን ሸክፈው ወዳመቻቹት ሌላ ሃገር እብስ ማለታቸውም የማይቀር ሃቅ ነው።

ሁለተኛው ምክንያት ግን ወያኔ ስልጣን ላይ የሚቆየው በትግራይ ህዝብ ድጋፍ ብቻ እንደሆነ በደንብ መረዳቱ ነው። ለዛም ሲል ያንን ክልል በሚታዩ ጥቅማጥቅሞች በመደለል እሱን እንዲያመልክ ለማድረግ ይሞክራል። የሚገርመው ነገር ፊታቸውን አዙረው ደግሞ (የመንግስት መገነኛ ብዙሃን ሳይቀሩ) ትግራይ ውስጥ ልዩ የልማት እንቅስቃሴ እንዳለና ሰፊ የህዝብ ድጋፍ እንዳላቸው ለሌላው ህዝብ በመጠቆም ጥላቻና ልዩነትን ይዘራሉ።

አይ ይሄ ትክክል አይደለም። የትግራይ ክልል ህዝብ እንደውም ከሌላው የበለጠ ተበድሏል የሚል ካለ፡ ታዲያ ለምን ጥያቄ አያነሳም? ሌላው ተበደልኩ ብሎ እሪ ሲል ቢያንስ በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ካለ ለምን አይታገልም? የተበደለ ህዝብ እንዴት ዝም ይላል?

### *ሐ) የትግራይ ህዝብ ወርቅ ነው ይሉታል*

ገገርዎቹ የስልጣን እድሜያቸውን ለማራዘም የትግራይ ህዝብ ላይ በስነልቦናም ሳይቀር ሙጥኝ እንዳሉ ግልጽ ነው። ትግሬውን የተለየህ ምርጥ ዘር ነህ ይሉታል። አንተ ከሌሎቹ ወንድሞችህ የተለየህ ጀግና ህዝብ ነህ ይሉታል።

በርግጥ የትግራይ ህዝብ ወርቅ ሊሆን ይችላል፡፡ መዳብ ወይም አሉሚኒየም ወይም ዚንክ ወይም ፋንድያ የሆነ ኢትዮጵያዊ ግን የለም። ወንድማማቾች ነን ካልንም አንድ ነን ማለት ነው። አንተ ከሌሎቹ ወንድሞችህ የተለየህ ወርቅ ነህ ሲባል፡ "እንዴት?" ብሎ መጠየቅ ከትግራይ ህዝብ ይጠበቃል። ምክንያቱም የተፈለገው ነገር እኛ በዘር የበላይነትና የበታችነት ስንናጭ እሱ ስልጣኑን ማራዘም ብቻ ነው።

ትናንት ወንድሞቻችን ከነበሩት ኤርትራውያን ጋር አለያይተው ዛሬ የምስራቅ አፍሪካ እስራኤልና ፍልስጤም አድርገውናል። ሻቢያና ወያኔ የኤርትራን ህዝብም አንተ የተለየህ ምርጥ ህዝብ ነህ ይሉት ነበር። ኤርትራውያንን ከትግሬ ወንድሞቻቸው እንኳን ሳይቀር የበለጡ ወርቅ እንደሆኑ ይነግሩዋቸው ነበር (ምናልባት አሁን አልማዝ ሆነው ካልሆነ!)። ዛሬ ደግሞ ተራው የትግራይ ህዝብ ነው። እነመለስ ይሄንንም ህዝብ ለመለየት የማይምሱት ጉድጓድ የለም። በእርግጥ ህወሃት አነሳሱ የትግራይን ህዝብ ነጻ ለማውጣት ነበር። የሚገርመው ግን ስሙን እንኳን እስካሁን አለመቀየሩ የሚያብከነክነው ስንቱ፣ ትግሬ ይሆን? አንቀጽ 39 ላይስ ለምን ሙጭጭ ማለት ተፈለገ ብሎ የምር የሚጠይቅ ስንቱ ይሆን? ይሄ ለሌላው ህዝብ የሚያስተላልፈው መልክት ራሱ ከባድ ነው። ወያኔ ሁሉም ነገር ከቁጥጥር ውጭ ሲሆንበት የትግራይ ወግናችንን ለመገንጠል እያደባ ነው ወይ የሚል ስጋት በብዙ ሰዎች ልብ ውስጥ ይፈጥራል።

እንደኔ እንደኔ አንድ ነጻ አውጪ ነኝ ባይ ቡድን ነጻ አወጣዋለሁ ከሚለው ህዝብ ድጋፍ ካላገኘ የትም እንደማይደርስ ይታወቃል። ቁም ነገሩ ያለው የትግራይ ህዝብ ከሌላው ህዝብ በተለየ ተጨቁኛለሁ፣ ከጭቆናም ነጻ ለመውጣት ህወሃት መፍትሄ ነው፣ ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍል እስከመለየት ቢያደርሰኝም ብሎ አምኖበት ከሆነ ያ ሌላ ጉዳይ ይሆናል። ያለበለዛ ነጻ ላወጣህ ነው ብሎ ከወገኖቹና ከእናት ሀገሩ የሚለየውን እንደ ህወሃት አይነቱን ዘረኛ ቡድን ዘወርበል ሊለው ብቻ ሳይሆን አምርሮ ሊታገለው ይገባል። የትግራይ ህዝብ ይሄንን ጉዳይ አሁንም የምር ሊያስብበት ይገባል ባይ ነኝ።

### *መ) የትግራይ ህዝብ የወያኔ ሰይጣናዊ ፕሮፓጋንዳም ሰለባ ነው - ይበላሃል ጅቦ!*

ለዘመናት ከወንድሞቹ ጋር አብሮ የኖረን ህዝብ ፣ በደሙና በአጥንቱ ኢትዮጵያን የገነባ የትግራይ ህዝብ ዛሬ እነመለስ እኛ ከሌለን ዘርህን ከምድረ ገጽ ሊያጠፉት አሰፍስፈዋል ይሉታል። እራሳቸውን የትግራይ ህዝብ መተንፈሻ አካል አድርገው ስለዋል - እነሱ ከሌሉ

የትግራይ ህዝብ ይሞታል! ስለኢትዮጵያ አንድነት በጮህን ቁጥር ወያኔ ነፍጠኞችና የደርግ ርዝራዦች መጡባችሁ እያለ የትግራይን ህዝብ ያስፈራራል። ፊቱን አዙሮ ሌላውን ህዝብ ደግሞ እኛ ከሌለን ኢትዮጵያ የለችም በብሄር ትበጣጠሳለች ይለዋል።

በተለይ በ1997 ምርጫ ወያኔ ስልጣኑን እንደሚያጣ ሲገባው፡ የኢንተርሃምዌይን ካርድ ስቦ ተጫወተ። የትግራይም ህዝብ የዚህ ሰይጣናዊ ፕሮፓጋንዳ ሰለባ ሆነ። በገጠርም በከተማው አፍንጫህን ላስ የተባለው ወያኔ ትግራይ ውስጥ በ99% ድምጽ አሸነፍኩ አለን።

እውነታው ግን ያ አልነበረም። ሲጀምር የኢትዮጵያ ህዝብ እንደነ በረከትና ስብሃት ጨካኝና አውሬ አይደለም። እነሱ የትግል አጋሮቻቸውንና ወንድሞችቻቸውን ሳይቀር ከበረሀ ጀምሮ እየበሉ ስለመጡ ሌላውም ሰው እንደነሱ ነፍሰ በላ ነው ማለት አይደለም። ህዝቡ ጠላቶቹንም ጠንቅቆ ያውቃል። ሲቀጥል መለስና ጸረ ህዝብ ቡድኑ ኖረም አልኖረም የትግራይ ህዝብ ቀርቶ የራሱ የመለስ ቤተሰቦችም ምንም አይሆኑም ነበር። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ህዝብ ሌላው ቢቀር ጨዋና ፈርሃ-እግዚያብሄር ያደረበት ህዝብ መሆኑን ወያኔ ራሱ በደንብ ያውቃል። የሚያሳዝነው ይችንም የማህበረሰብ እሴታችንን ሳይቀር ሊሸረሽርና ሊያጠፉ ግን ይታገላል።

ባጠቃላይ ከላይ የተቀመጡት ምክንያቶች አሳመኑም አላሳመኑም እውነታው ግን ትግራይ ክልል ውስጥ የሚኖር የትግራይ ተወላጅ እንደሌላው ኢትዮጵያዊ ይሄንን ግፈኛ፤ አፋኝና ገንጣይ ቡድን እየታገለ አይደለም። እየታገለ አይደለም ብቻ ሳይሆን፡ ኢትዮጵያችን ላይ ለሚፈጽመው ጥቃት መንጠላጠያ ሆኗል።

## *2) ከትግራይ ክልል ውጭ ያለው የትግራይ ተወላጅ*

ከትግራይ ክልል ውጭ በሌሎቹ የኢትዮጵያ ግዛቶች የሚኖረውን የትግራይ ተወላጅ በሶስት ማስቀመጥ ይቻላል።

### *ሀ) የትግሬ ወያኔዎች* - ወያኔ ትግሬ ነው!

መቼም ወያኔ መለስና ስብሃት ብቻ ናቸው ካልተባለ በቀር በወያኔ የስልጣን መዋቅር ውስጥ ከሞላ ጎደል ፈላጭ ቆራጭ የሆኑት የትግራይ ልጆች እንደሆኑ ይታወቃል። ከነመለስ ጀርባ ሆነው የነሱን ሰይጣናዊ ሃሳብ የሚተገብሩ የትግራይ ባለሟሎች አሉ። ትግሬ በሙሉ ወያኔ ባይሆንም ወያኔ ግን ትግሬ ነው። እነዚህ 10ም ይሁኑ 20፡ 50 ይሁኑ 100፡ ሀገር እያፈረሱ፡ ህዝብ እያስለቀሱና እየዘረፉ ያሉ ናቸው። አዲሱንና አባዱላን የመሳሰሉ ከብቶች ከኋላ ጠምደው የሚያርሱት እነሱ ናቸው። ህዝቡን በዘር ከፋፍለው የሚያፋጁት እራሳቸው ናቸው። በትግራይ ህዝብ ስም በሚልዮኖች የሚቆጠር ብር ዘርፈው አስቀምጠዋል። ቀን የጎደለ እለት እግሬ አውጭኝ ማለታቸውም አይቀርም - አንዳንዶቹም እያደረጉት ነው።

አለመታደል ሆኖ እንጂ የሀገሩ ጉዳይ የሚያንገበግበው አንድ ሁለት ጀግና ከወያኔ መሀል ቢኖር ለራሱም ታሪክ በሰራ፡ ለህዝቡም የስቃይ ዘመን ማጠር ምክንያት በሆነ ነበር። መቼም በግል ቂም በቀል ክንፈን መግደል ከተቻለ፡ ለሃገሩ የምር የሚቆረቆር ወንድማ ስንት ተአምር በሰራ!

እነ መለስና በረከት ለሻቢያ ያደላሉ ፣ አሰብን አሳጥተው ጉሮሮአችንን ዘጉት፣ የሀገር ፍቅር የላቸውም እያሉ ሁልግዜ ከመብከንከንና ከማላዘን እውነት እናቱ የወለደችው ወንድ የትግራይ ልጅ በቤተመግስቱ አካባቢ ካለ ሜዳውም ፈረሱም በእጁ ነው። መቼም ሞት ለሁሉም አይቀርም። በነመለስ እንደ ሸንኮራ ተመጠ ከመጣል፤ ለሃገርና ለወገን የሚበጅ ታሪክ ሰርቶ ማለፍ ዘላለማዊ ክብር አለው። አብሮት የተዋደቀውንና ከሞት ያተረፈውን ስዬን በሃሰት ክስ እንደ አይጥ እስርቤት ወርውሮ ያሰቃየ፡ አንተ ማነህና ነገ ላንተ ይመለሳል?

### *ለ) አፍቃሪ ወያኔ - ቅርንጫፍ ወያኔ*

እነዚህኞቹ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ትግሬ በመሆናቸው ብቻ እየተጠቀሙ ያሉ በዚህም ምክንያት ወያኔን የሚደግፉ ናቸው። እነዚህ ከቀበሌ እስከ ክልል ፣ ከመንግስት ተቋማት እስከ ግል ድርጅት ፣ ከኮንደሚንየም ቤት እስከ መሬት ባለሃብትነት፤ ከሙያ ማህብራት እስከ ትምህርት ተቋማት ድረስ ባሉ ቁልፍ ቦታዎች በጉልበትም በጸባይም፤ በእውቀትም ያለእውቀምት፤ የተሰገሰጉት ትግሬዎች ናቸው።

”የወጌሻ ልጅ ዛፍ ላይ ያድራል” እንደሚባለው ሌላው ህዝብ አገር ውስጥ መኖር አቅቶት ስደትን እንደ ጽድቅ በሚመኝበት ወቅት፤ እነሱ ኢንቨስተር ናቸው፤ እነሱ ባለ አዳዲስ ሞዴል መኪና ባለ ቤቶች ናቸው፤ እነሱ ነጋዴዎች ናቸው ወዘተ። ትናንት ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ ይገፉ የነበረ የከተማ ትግሬ ዛሬ ቢጠሩት የማይሰማ ሚሊየነር ሲሆን ፤ የተለየ ችሎታ ወይም እውቀት ሳይኖረው የትላንት ጎረቤታችን ዛሬ የቀበሌያችን ንጉስ ሆኖ ህዝብ ሲያሰግድ ፤ አብረን የተማርናቸውና የእውቀት ደረጃቸውን ጠንቅቀን የምናውቃቸው የትግራይ ጎሳ ተወላጆች የመንግስት መስሪያቤቶችን እንዳሻቸው ሲያሽከረክሩና ስልጣን ሲቆናጠጡ ወዘተ በአይናችን በብረቱ እያየን ነው።

እነዚህ በብዛት የወያኔ ካድሬዎች ናቸው። በገንዘብ ይረዳሉ ፣ ህዝብ ይሰልላሉ ፣ የወያኔን መመርያም ያስፈጽማሉ። እነዚህ ናቸው እንግዲህ ብዙ ግዜ ”ትግሬ በሙሉ ወያኔ ነው ወይ? ” የሚል ብዥታ ውስጥ የሚከቱን።

በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩትም የስነልቦና ጫና ከፍተኛ ነው። በተለይ በከተማዎች አካባቢ በትግርኛ አንደበት አማርኛ የሚያወራ ሰው የፈለገውን ነገር ያሻው ቦታ ሂዶ ማድረግ ይችላል። ትግርኛ መናገር በራሱ የደህንነት መታወቂያ ነው - ማንም አይነካውም እሱ ግን የፈለገውን ማድረግ ይችላል። ባጭሩ ኢትዮጵያውያን በገዛ ሀገራቸው ሁለተኛ ዜጋ ሆነዋል። ይሄንን ጸሀይ የሞቀው ሀቅ አለባብሰን ብናልፈው ነገ ከፍተኛ ችግር ያስከትላል።

እነዚህ የትግራይ ተወላጆች ናቸው በየአካባቢያቸው የሚፈሩትም፤ ውስጥ ውስጡን ደግሞ የሚጠሉትም። ወያኔ እርስ በርሳችን እንድንጋጭ መንገዱን እየጠረገልን ሲሆን እነዚህ ደግሞ የከተማ ትግሬዎች ሂደቱን እያገዙ ነው። እራሳቸው የአካባቢያቸው ህዝብ እንዲጠላቸው ካደረጉ በኋላ የተጠላነው ሌላው ህዝብ ዘረኛ ስለሆነ ነው ማለትም አያዋጣም። አስቀድሞ ማሰብና መጠንቀቅ ያስፈልጋል። አለበለዚያ የሚፈጠረው ችግር ብዙ ዋጋ የሚያስከፍለን ይሆናል። ለህሊናችን እንኳን መኖር ቢያቅተን ለነገና ለልጅ ልጆቻችን ማሰብ እንዴት ይሳነናል?

### *ሐ) ንጹህ ሀገር ወዳድ ትግሬ*

በዚህ ካቴጎሪ ውስጥ ያሉት ለሃገር፤ ለህዝብና ለታሪክ ተቆርቋሪ የሆኑ ብዙዎቹ ትግሬዎች ናቸው። እነዚህ ከወያኔ ጋር ግንኙነት የላቸውም። ምን አልባትም የበለጠ ተጎጂ ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን ወያኔ ከወረደ የባሰ ይመጣል በሚል የይበላሃል ጅቦ ፕሮፓጋንዳ ሰለባነት ዝምታን የመረጡ ናቸው። እነዚህኞቹ የወያኔን የዘርና የአምባገነንነት ፖሊሲ የማይወዱና የሚኮንኑ ሆኖም በጸረ ወያኔ እንቅስቃሴ ጉልህ ሚና የማይጫወቱ ናቸው።

እውነት ለመናገር በጣም ብዙ ትግሬዎች ወያኔን እየጠሉም ነገር ግን በፍርሃት ድባብ ውስጥ ሆነው በዝምታ እየኖሩ ነው። አንዳንዶቹም ቤተሰባቸውን ጠቅለው ከሀገር እስከመሰደድ የሚመኙም፤ ያደረጉም አሉ።

የነዚህኞቹ ንጹሃን ጭንቀት ግልጽ ቢሆንም ዝምታና ሽሽት ግን በፍጹም መፍትሄ ናቸው አልልም። እነሱም እንደሌላው ኢትዮጵያዊ የወያኔን ግፍ ለማስቆም መታገል አለባቸው ብዬ አምናለሁ። ለእውነት መቆምና መሞት የትግራይ ህዝብ ጥንት ሲያደርገው የነበረ ነው። ዞሮ ዞሮ ችግሩ ለሀገርና ለህዝብ ከሁሉም በላይ ደግሞ ለልጅ ልጅ ሳይቀር የሚተላለፍ ነውና፡ ዝምታ በጭራሽ መፍትሄ አይሆንም። በተለይ የዚህ አይነት ስሜት ያላቸው የትግራይ ምሁራን ኢትዮጵያን ለማዳንና ከታሪክ ተወቃሽነት ለመዳን ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል።

## *ማጠቃለያ*

*መሪዎች ያልፋሉ። ግለሰቦችም ይሞታሉ። ሃገር ግን ለዘላለም ትኖራልች። የትግራይ ህዝብ በቸልተኝነትም ይሁን በመተባበር በሌላው ህዝብ ላይ ለሚፈጸም ግፍና በደል የታሪክ ተወቃሽ መሆን የለበትም የሚል እምነት አለኝ። በስሙም የሚነግዱትን ወያኔዎች በቃችሁ ሊሏቸው ይገባል። አሁንም አልረፈደም። እናት ሃገራችን ዘርና ሃይማኖት ሳይለይ የሁሉኑም ልጆቹዋን ትብብርና አንድነት የምትሻበት ወቅት ላይ ነች። አሁን ያለውን አስፈሪ ሁኔታ ተገንዝቦ ለመጪው ትውልድ ማሰብም ነቢይ መሆን አይጠቅም። ለማይቀረው ለውጥ አብሮ መታገሉና እነዚህን አገር አጥፊዎች ማስወገዱ ግድ ይላል።*

ሰዎች በዘራቸው ሳይሆን በችሎታቸው የሚለኩባት ፣ በጎሳቸው ሳይሆን በስብእናቸው የሚመዘኑባት ፣ እያንዳንዱ ዜጋ ነጻነቱ የተረጋገጠባትና ፍትህ የሚያገኝባት ኢትዮጵያን መገንባት ከቻልን ኢትዮጵያችን ለሁላችንም ትበቃለች ብቻ ሳይሆን ለሌላም ትተርፋለች። ኢትዮጵያዊ ነን ከሚሉ በተግባር ግን ህዝቡን ከፋፍለው ሀገር እያፈርሱ ካሉ ጠላቶች ጋር በሚደረገው ትንቅንቅ የትግራይ ልጆች ታሪካዊ ሚና ለመጫወት የተሻለ እድል አላቸው እላለሁ - ነገ ሳይሆን ዛሬ!

***ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይጠብቅ!!! ለሁላችንም ልብ ይስጠን!!!***